# የሺናሻ፣ የሲዳማ፣ የመዠንገር እና የወላይታ ባህላዊ ህግ ጥናት ሪፖርት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ማዕረግ ገ/እግዚአብሄር

ይድነቃቸው ከበደ

ኢሳያስ አየለ

መስፍን እሸቱ

1 በየአካባቢው ግጭቶችን ለመፍታት በተለይ በገጠሩ አካባቢ አግልገሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ባህላዊ የግጭት መፍችያ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት እና ተቀባይነት ከግምት በማስገባት (አሁን በስራ ላይ ባለው የኢፌድሪ ህገ መንግስት እውቅና የተሰጣቸው ቢሆንም) የባህላዊ ህጎችንና የባህላዊ ተቋማትን አሰራር በተመለከተ ዝርዝር ህግ በህግ አውጪው አለመውጣቱ በአፈፃጸም ረገድ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ የህገ መንግስቱ አላማና ፍላጎትም ሙሉ በሙሉ እንዳይተገበር አድርጎታል፡፡ በመሆኑም የህግ አውጪው አካል ዝርዝር ህግን በማውጣት ይህን ችግር ሊፈታው ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ ሩቅ ሳይኬድ በአህጉራችን ከሚገኙት ሀገራት መሃከል የደቡብ አፍሪካ የዛምቢያ የቦትስዋና እና የሴራሊዮን ህገ መንግስት እና የህግ ስርአቶች በዚህ ዙሪያ የወሰዱትን አቋም መመልከቱና ልምድ በመቅሰም ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛነቅ ለችግሩ መፍትሄ መሻት ያስፈልጋል፡፡ይህ ጥናት ማንኛውም የወንጀል ጉዳዮች በባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት መታየት አለባቸው የሚል አቋም የለውም፡፡ የባህላዊ ህግ እና የፍትህ ተቋማቱ አደረጃጀት ለምሣሌ ያህል፡

- እጅግ ውስብስብ እና የባለሙያ ዕውቀት የሚጠይቁትን በተላላፊ የገንዘብ ሰነዶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን፣
- የሃገርንና የመንግስትን ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥለውን የሙስና፣ የኮንትሮባንድ እና ማኒ ላውንድሪ ወንጀሎችን፣
- የሽብርተኝነት፣ የዝርፊያ፣ የስርቆት እና የሃገር መክዳት ወንጀሎችን፣
- ከቴክኖሎጂ ዕድገትና ምጥቀት ጋር (ለምሣሌ ከኮምፒውተር አጠቃቀም) ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን፣
- በአለም አቀፍ ህግ ይቅርታ የማያሠጡ ወንጀሎችን፣
- በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወሲብ ነክ እና የመሣሠሉትን ለመዳኘት የሚያስችል ዘመናዊ አደረጃጀት፣ ዕውቀትም ሆነ ብቃት ላይኖራቸው ይችላል፡፡

እንደ እነዚህ አይነት ወንጀሎችን የመዳኘት ሥልጣን ይሠጣቸው ቢባልም ተገቢ ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ከዚህ እና ከመሣሠሉት የወንጀል ድርጊቶች ባሻገር፡-

- በጎሣ በብሔር እና በሃይማኖት ተከታዮች መሃከል የሚነሱ ግጭቶችን፣
- በግድያ ምክንያት የሚከሰቱ ቅራኔዎችን፣

- በቤተሰብና በውርስ ጉዳዮች የሚነሱ አለመግባባቶችን
- በድንበር፣ በመሬት አጠቃቀም፣ በጋራ የግጦሽ፣ የውሃ እና መሰል የተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም እና የይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለዘለቄታው እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት ባህላዊው የፍትህና የህግ ተቋም ከመደበኛው የፍትህ ተቋማት የበለጠ ተመራጮ ናቸው፡፡ የባህላዊ ህግ እና የፍትህ ተቋማቱን የስልጣን ዝርዝር እና አሰራርን በተመለከተ በተለይ የወጣ ህግ ባይኖርም እና ከላይ የተመለከቱት ወጀሎችን የማየት ስልጣን ያላቸው እንደሁኔታው የመደበኛ ፍርድ ቤቶች እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ቢሆንም አብዛኞቹ ከላይ የተጠቀሱት እናመሰል ቅራኔዎች በአብዛኛው እየተፈቱ ያሉት በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ እና በእርቅ ነው፡፡

በመሆኑም መደበኛው የፍትህ አካላት የሚያከናውኑትን ባህላዊ የፍትህ ተቋማትና እና የሃገር ሽማግሌዎች በተሻለ ውጤታማ እና ዘላቂ ሠላም በሚያመጣ መልኩ እየፈቱት ያለ መሆኑ በተጨባጭ እየታየ ከሆነ ስራቸውን የበለጠ ሊያቀላጥፍ የሚችል ዝርዝር ህግ እስካሁን ላለመውጣቱ ለባህላዊ የፍትህና የህግ ተቋማቱ ተገቢውን ትኩረት እና ቦታ ካለመስጠት የዘለለ ሚዛን የሚደፋ ምክንያት ማቅረብ አዳጋች ይመስላል፡፡ ስለዚህም ህገ-መንግስቱን መሠረት አድርጎ ይህንን የሚመለከት ዝርዝር ህግ በህግ አውጪው ሊወጣ ይገባል፡፡

ከዚህ በፊትም ሆነ ወደ ፊት በባህላዊ ህግ ዙሪያ ለተደረጉት እና ለሚደረጉት ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተለይም በዚህ በኩል የትኞቹ የባህላዊ ህጎች እና ቷቋማት ናቸው ጠቃሚዎቹ? ህገ መንግስቱ ካስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆች ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉት እንዴት ነው? ባህላዊው ህግና መደበኛው የህግ እና የፍትህ ስርአት እንዴት ሊመጋገቡ ይችላሉ? ወዘተ... የሚሉትን በስፋት መርምሮ ጠቃሚ የሚባሉትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከአካባቢ ባህላዊ የግጭት መፍቺያ ተቋማት ውስጥ ግጭቶችን በመፍታት የጎላ ልምድ ያላቸውን የሀገር ሽማግሌዎች በመምረጥ የህግ፣ የፖለቲካ ሳይንስ፣ የታሪክ፣ የአንትሮፖሎጂ፣ የስነ ህዝብ ወዘተ ምሁራንን ያቀፈ ውይይት እና አገር አቀፍ ኮንፈረንስ በማዘጋጀት ብሄረሰቡ አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ግጭትን የሚፈታበት፣ የማህበረሰቡን የፍትህ አመለካከት እና አተያይ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ የግጭት መከላከያ እና መፍቻ ደንብ ከሀገሪቷ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታ ጋር እየተገናዘበ በፖሊሲ ደረጃ የሚቀረጽበት ስልት መቀየስ እና ይህንንም ገቢራዊ የሚያደረግ ተቋም የሚቋቋምበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የዚህ ተቋም የባህላዊ ህግ ጥናት ቡድን

“የደቡብ ብሔሮች፣ ብሄረሰቦች ምክር ቤት” እና የጋምቤላ ክልል “የሀገር ሽማግሌዎች ምክር ቤት” አርአያ እና መነሻ ሊሆን የሚችል ትልቅ ተግባር እያከናወኑ መሆኑን ለመረዳት ችሏል። በመሆኑም ይህ አይነቱ ጥረት በሌሎች ክልሎችና በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊተገበሩ እና ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።

ግጭቶችን አስቀድሞ የመከላከል እና ሲከቱም በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሚሆነው የህዝብ ተሳትፎ ሲኖር ነው። የማህበረሰቡ ወይም የህዝቡ ተሣትፎ መኖር የባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአት አይነተኛ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ያሉ የፖለቲካው ስርአትና የመደበኛው የፍትህ አካላት ግጭቶችን እንዴት መከላከል እና መቆጣጠር ብሎም መፍታት እንደሚቻል በግጭት ፈቺነት ከሚሳተፉት የሃገር ሽማግሌዎች ምክር የሚያገኙበትን አደረጃጀት፣ መዋቅር እና አሰራር መፍጠር።

እያንዳንዱ ግጭት የራሱ ባህርይና መንስኤ እንዳለው በመረዳት ከግጭቱ ዓይነትና ከህዝቡ ባህል አንፃር እየታየ ከአካባቢው ባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ይበልጥ የሚዳብርበትን ሁኔታ መፍጠር እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች እና ከምንጊዜም በላይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡